# ቅመምና ቤተሰቡዋ



25-28ኛው ሳምንት

1ኛ ክፍል

መጽሐፍ 10

# ቅመምና ቤተሰቡዋ

መጽሐፍ 10 | 1ኛ ክፍል | 25-28ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ።

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ቅመምና አለሙ ባልና ሚስት ናቸው።

አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጅ አሉዋቸው፡፡ ወንዱ ከበደ፣ ሴቲቱ አልማዝ ይባላሉ፡፡ አራቱም የቤተሰብ አባላት በአንድ ላይ ይኖራሉ፡፡



አለሙ በርበሬ ይነግዳል።
ቅመም በንግድ ስራው
ታግዘዋለች።



ከበደና አልማዝ ይማራሉ::
የቤተሰቡ አባላት በየተራ
ምግብ ያዘጋጃሉ::

አለሙና ቅመም ጠንካራ ሰራተኞች ናቸው:: ልጆቻቸው በትርፍ ጊዜያቸው ያግዙዋቸዋል:: በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ከበሩ:: የቤት መኪናና ዘመናዊ የመኖሪያ ቤት ገዙ::



የቤተሰቡ አባላት ቅን፣
አሳቢና ደግ ናቸው።
ቅመምና ባለቤትዋ ለተቸገሩ
ገንዘብና ልብስ ይረዳሉ።



ችግረኛ ተማሪዎችን ይረዳሉ።
ለተማሪዎቹ ደብተር፣ እርሳስና
እስክርቢቶ ይገዙላቸዋል።



በሚሰሩት በጎ ተግባር
በጣም ታወቁ። በመንግስትና
በአካባቢው ህዝብ ተመሰገኑ።
ተሸላሚም ሆኑ።

USAID
ከአሜሪካን ህዝብ